# ብፁዕ አቡነ መርቆርዮስ የተባረሩበት ሚስጥር ወጣ

ከአቶ ሲሳይ አገና የኢሳት የዜና ትንተና

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤትን ሰነድ በመረጃ መረብ ለዓለም እየበተነ ያለው ዊኪ ሊክስ ስለኢትዮጵያ ሰሞኑን የለቀቀው ማስረጃ እጅግ የበዛ ሲሆን አሁን ከቤተ - መንግስት ወደ ቤተ - ክርስቲያንም አምርቶል።

የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ፓትሪያክ አቡነ መርቆርዮስ በመንግሥት በትዕዛዝ መባረራቸውን የዊኪ ሊክስ ሰነድ አጋልጧል። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ታምራት ላይኔ ለአሜሪካው አምባሳደር ይህንኑ አረጋግጠዋል። ረቡዕ ጃንዋሪ 5 2009 በኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር ታህሳስ 27 2001 የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ታምራት ላይኔ በአዲስ አበባ የአሜሪካን አምባሳደር ከነበሩት ሚስተር ዶናልድ ያማማቶ ጋር መገናኘታቸውን ሰሞኑን ይፋ የሆነው ሚስጥራዊ የሆነ ሰነድ ያስረዳል። ሚስተር ዶናልድ ያማማቶ አቶ ታምራትን ያገኙት አቶ ታምራት የ12 ዓመታት የወህኒ ቤት ቆይታቸው አጠናቅቀው በወጡ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንደሆነም ተመልክቷል። አቶ ታምራት ከአምባሳደር ያማማቶ ጋር ጃንዋሪ 5 2009 ያደረጉትና ከ8 ቀናት በኋላ ጃንዋሪ 14 2009 ወደ አሜሪካ የተላከው ሚስጥራዊ ሰነድ አቶ ታምራት ስልጣን ላይ ላለው ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ (ሕወሐት) እንዲሁም ለኢሕአደግ ታማኝ እንደነበሩ በማስታወስ ይንደረደራል።

በእስር ቤት ቆይታቸው ክርስቲያን ሆነው መውጣታቸውን ከአመጽ መንገድ ርቀው የሰላም ሰው ሆነው መውጣታቸውን ለአምባሳደሩ ገልጸዋል። የእስር ቤት አያያዛቸው ጥሩ እንደነበረ መናገራቸውም ተመልክቷል። በጃንዋሪ 2009 መጀመሪያ አሜሪካ ከአምባሳደር ጋር የተወያዩት ታምራት ላይኔ በዚያው ወር መጨረሻ አሜሪካን ሐገር ዴንቨር ከተማ የሚገኙትን ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን ለማየት እንደሚሄዱና የሕክምና ምርመራ በዚያው እንደሚያደርጉ ለአምባሳደሩ ገልጸዋል። ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማድረግ የሚችሉትን ነገር ለማድረግ ማቀዳቸውን ይህም በዋናነት ኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ ፍቅር እንዲሰፍን የሽምግልና ሚና እንደሚሆንም አስረድተዋል። እግዚአብሔርን ማገልገልም ሌላው ኃላፊነታቸው መሆኑን ተናግረዋል።

በአሰሯቸው ሰዎች ቂም አለመያዛቸውን ይልቁንም ወዳጅነታቸው መቀጠሉን ለዶናልድ ያማማቶ የተናገሩት አቶ ታምራት ላይኔ ከእስር መልስ በርካታ የሕወሐት ፓሊት ቢሮ አባላት በመንግስቱ ኃላፊነት በመሰላቸት እንዲሁም ከጤና ጋር በተያያዘ ሥልጣን ለመልቀቅ እንደሚፈልጉ ነግረውኛል ብለዋል። <u>ሆኖም ሥልጣኑን ተቃዋሚዎች ቢይዙት ሕገ-መንግስቱን እንደማይንዱ ሐገሪቱንም እንደማያፈርሱ እምነት የለንም በሚል ስልጣኑን ሙጥኝ ማለታቸውን እንደነገሯቸው ለያማማቶ አስረድተዋል።</u> በመሆኑም ሕወሐት ተተኪ አመራር በማሰልጠን ላይ መሆኑን አቶ ታምራት አስረድተዋል። ስልጠናውን በዋናነት አይዲዎሎጂን መሰረት ያደረገ እንደሆነም አመልክተዋል። የኢህአደግ አባልና የሕወሐት አጋር ፓርቲዎች ሚና እዚህ ጋር አልተጠቀሰም። አቶ ታምራት ይመሩት ስለነበረው በአዴንም ጭምር።

አቶ ታምራት ከእስር ለተፈታው ከወንድሙ ወገን የሆኑ ብዙ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ ፓለቲካ ተመልሼ የማግባባት የማስታረቅ ሚና እንድጫወት ጠይቀውኛል ሲሉ ለአምባሳደሩ ሲናገሩ አምባሳደር ያማማቶም በመንግስትና በተቃዋሚዎች እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሽምግልና ሚና ከተጫወቱ ኢምባሲው ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው ቃል እንደገቡ በሚስጥራዊው ሰነድ ላይ ተመልክቷል። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር ከታምራት ላይኔ ከሁሉ በፊት በሐይማኖት አባቶች ማለትም በአዲስ አበባና በአሜሪካ መካከል ባሉት መካከል እርቅ እንዲፈጠር ጥረት እንደሚያደረጉ አመልክተዋል።

<u>ሕጋዊ ፓትሪያርክ አቡነ መርቆሪዎስ ከስልጣን እንዲወርድና የቤተ-ክርስቲያኑ አባቶች ለሁለት እንዲከፈሉ ምክንያት የሆነውን ፊርማ ያሳረፍኩት እኔ ነኝ ሲሉ ለአምባሳደር ዶናልድ ያማማቶ አረጋግጠዋል። አቶ ታምራት በማን ውሳኔ እንደፈረሙ ግን አልገለጹም። ፓትሪያርኩ አቡነ መርቆሪዎስ እንዲወገዱ ውሳኔውን ያሳለፈው ሕወሐት በተናጥል ይሁን ኢህአደግ እንደ ስብስብ አቶ ታምራት አላብራሩም።</u>

የፓትሪያርክ አቡነ መርቆሪዎስ ከስልጣን መነሳት ሕገ-ወጥና የፓለቲካ ጣልቃ ገብነት ነው በሚል በአባቶችና በመዕመናን መካከል ጥያቄ ሲነሳ ቆይቷል። ፓትሪያርኩ በአቶ ታምራት ላይኔ ፊርማ እንደተወገዱ በውጭ የሚገኙ የቤተ-ክርስቲያን አባቶች ሲገልጹም ቆይተዋል።

በፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ ወገን የቆሙት ደግሞ በነሐሴ ወር 1983 ታትሞ በወጣው ድምፀ-ተዋሕዶ ጋዜጣ በአስረጅነት ይጠቅሳሉ። ድምፀ-ተዋሕዶ ላይ የወጣው ዘገባ ብፁሕ ፓትሪያርኩ በጤንነታቸው መታወክ ምክንያት ሥራውን ቅዱስ ሲኖዶሱ እንዲሰራ ጠየቁ። ቅዱስ ሲኖዶሱም ውሳኔ ሰጠ ይላል።

<u>ነሐሴ 28 ቀን 1983 የወጣው የቅዱስ ሲኖዶስ መግለጫ አቡነ መርቆሪዎስ በጠየቁት መሰረት ከስልጣን ወርደዋል በማለት የተጠቀመበት የጽሁፍም ሆነ የሰነድ ማስረጃ አልነበረም። የቀረበው ምክንያት መታተመማቸውን በቃል ነገሩን የሚል ነበረ።</u>

የዊኪ ሊክስን ዘገባ የተመለከቱ እንዳንድ ለቤተ-ክርስቲያኒቱ ቅርብ የሆኑ ወገኖች ከ20 ዓመታት ቦኋላም እውነቱ አደባባይ መውጣቱ የቤተ-ክርስቲያኒቱን ችግር ለመፍታት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንደሚኖረውም ያምናሉ።

ፓትሪያርክ አቡነ መርቆሪዎስ ለፓትሪያርክነት የተመረጡት ነሐሴ 28 ቀን 1980 ሲሆን ኢህአደግ ወደ ሥልጣን ላይ መምጣቱን ተከትሎ በነሐሴ 1980 አቶ ታምራት እንዳረጋገጡት ተገደው ስልጣናቸውን ለቀቁ። ላለፉት 20 ያህል ዓመታት ያህል በስደት አሜሪካ ውስጥ ይገኛሉ። ዛሬም ሕጋዊ ፓትሪያርክ እሳቸው ናቸው የሚሉ ጳጳሳት ከእሳቸው ጋር በመሆን ሐይማኖታዊ ተግባራቸውን ቀጥለዋል። በአቡነ ጳውሎስ የሚመሩትም በሐገር ቤት መንፈሳዊ ሥራቸውን እያከናወኑም

ይገኛሉ። ሁለቱም ወገኖች አስማምቶ ወደ አንድ ወገን ለማምጣት የሽምግልና ጥረቶች ቀጥለዋል።

**መረጃዎች**

http://www.cablegatesearch.net/cable.php?id=09ADDISABABA86
http://www.youtube.com/user/ESATelevision?blend=3&ob=5#p/u/21/su9aPUsm4Uc

ESAT news analysis 09 September 2011 wikliks about E thiopia orthodox.mpg የሚለውን በጉግል ይፈልጉ።

**ማሳሰቢያ**
**የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን (ኢሳት) ከማንኛውም ፓርቲ ያልወገነ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም ፍትሕና ዲሞክራሲን ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን የሕዝብ አይንና ጆሮ በመሆን የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል። ይህን ጥረት ለማገዝ www.ethsat.com ይጎብኙ።**